የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
አዲስ አበባ መስከረም ፳፫ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Sixth Year No.56
ADDIS ABABA October 3, 2013

**ማውጫ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ደንብ…………………………………ገጽ ፮፻፸፩

**CONTENT**

Addis Ababa City Government Kotebe University College Regulation…………………………………page 671

## ደንብ ቁጥር ፶፮/፪ሺ፮

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅን ለማቋቋም የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና የአለማቀፉ ማህበረሰብ መቀመጫ ከመሆኑ አኳያ ብዙ ስለሚጠበቅበት አንገብጋቢ በሆኑና የከተማው አስተዳደር ቁልፍ የትምህርትና የምርምር አግባብነትና ጥራት ችግሮች መፍትሄዎች ላይ በማተኮር የከተማውን ብሎም የአገሪቱን ሕዝቦች የሰላም፣ የዲሞክራሲና የልማት ፍላጎትን ለማሳካት ብቃት ያለው አስተዋጽዖ የሚያበረክት የራሱ የሆነ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንዲኖረው በማስፈለጉ፤ የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአሁኑ ወቅት ከሚያካሂዳቸው የትምህርት ፕሮግራሞች በተጨማሪ የወደፊቱን የከተማ አስተዳደሩንና የአገሪቱን የሰው ኃይል ፍላጎት መሠረት ወዳደረጉ የከፍተኛ ትምህርት፣ ሥልጠናና የምርምር ፕሮግራሞች

## Regulation No. 56/2013

## A Regulation to Provide for the Establishment of Kotebe University College in Addis Ababa City Government

**WHEREAS,** it has become necessary to have its own higher education institution, as much is expected of Addis Ababa City being the seat of the Ethiopian Federal Democratic Republic Government as well as the International community, that offers quality contribution towards achieving peace, democracy, and development aspiration of the people of the City as well as the Nation by focusing on pressing and key educational and research quality problems and solutions of the City;

**WHEREAS,** it has become appropriate to create a legal framework to expand the current programmes of Kotebe College of Teacher Education to those higher education, training and research programmes inline with the skilled

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ማስፋፋት እንዲቻል የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፤

ኮሌጁ በአሁኑ ወቅት በሰው ኃይልና በአስፈላጊ መሰረተ ልማቶች ጥራት ያለው የከፍተኛ ትምህርት መስጠት የሚችልበት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ በረጅም ጊዜ አገልግሎቱ ለአገሪቱም ሆነ ለከተማው አስተዳደር በትምህርቱ ዘርፍ ያበረከተውንና አሁንም እያበረከተ ያለውን አስተዋጽዖ እውቅና በመስጠት የተሟላ የከፍተኛ ትምህርት መስጠት የሚችልበት ሕጋዊ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤

የኮሌጁ ማቋቋሚያ አዋጅ በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. የወጣ በመሆኑ ረጅም ጊዜ በማስቆጠሩ ከዚያ በኋላ የወጡ የተለያዩ ሕጎችንና የከተማ አስተዳደሩንና የኮሌጁን ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ባገናዘበ ማቋቋሚያ ደንብ መተካት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለዉ ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም.አንቀጽ ፲፬ (፩) (ረ) እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፪) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

manpower needs of the City Government as well as the country;

**WHEREAS,** it become necessary to create an appropriate legal framework to make the college provide full-fledged higher education by considering the college being fully equipped with skilled and experienced manpower and facilities to provide quality higher education and acknowledging the contribution the college has made to the education sector of the country as well as the City through its long term service till now;

**WHEREAS,** it become necessary to substitute the establishment regulation of the college issued in 1998, long ago, with new one that complies with different laws issued later and considering the current situation of the City Government and the college as well;

**NOW, THEREFORE,** the Cabinet of Addis Ababa City Government pursuant to Article 14 (1) (f) of the Revised Charter Proclamation No. 361/2003 and Article 5(2) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009 has issued this Regulation as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፶፮/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Addis Ababa City Government Kotebe University College Establishment Regulation No.56/2013".

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩."**አዋጅ**" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶//፪ሺ፩ ነው፤

፪."**ቦርድ**" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ የተመለከተው የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአስተዳደር ቦርድ ነው፤

፫. **“ሚኒስቴር”** ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው፤

፬."**ሴኔት**" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ የተመለከተው የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሴኔት ነው፤

፭. **“ከተማ አስተዳደር”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፮. "**የአካዳሚክ ሠራተኛ**" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪(፫) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሠራተኛ ነው፤

፯. **“የትምህርት ክፍል”** ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪(፬) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካል ነው፤

፰. **“የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ”** ማለት የአስተዳደር፣ የቢዝነስ አመራር፣ የፋይናንስና የሂሳብ ሥራ፣ የምግብ አገልግሎት ማቅረብ፣ የጥገና፣ የጥበቃና ደህንነት ወይም የመሳሰሉትን ተግባራት የሚያከናውን የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሠራተኛ ነው፤

፱. "**የቴክኒክ ሠራተኛ**" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪(፲፭) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሠራተኛ ነው፤

፲. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

**2. Definitions**

In this Regulation unless the context demands otherwise:

1. **“Proclamation”** means the Higher Education Proclamation No.650/2009;
2. **“Board”** means the Administrative Board of the University College referred to in Article 8 of this Regulation;
3. **“Ministry”** means the Ministry of Education;
4. **“Senate”** means the University College’s Senate referred to in Article 10 of this Regualtion;
5. **“City Government”** means Addis Ababa City Government;
6. **“Academic Staff”** means the employee of the University College as defined in Article 2(3) of the Proclamation;
7. **“Academic Unit”** means the unit in the University College as defined in Article 2(4) of the Proclamation;
8. **“Administrative Support Staff”** means personnel of the University College employed to provide administrative, business management, accounting, catering, maintenance, safety, security and such other services;
9. **“Technical Staff”** means the employee of the University College as defined in Article 2(15) of the Proclamation;
10. Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## ክፍል ሁለት
## የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መቋቋም፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር

**፫. መቋቋም**

፩. □ተቤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ" እየተባለ □ሚጠራ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በሥሩ የሚከተሉትን ተቋማት፣ ፋኩልቲዎችና ትምህርት ቤቶችን ያካትታል፡-

ሀ. የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣

ለ. የተፈጥሮና ኮምፒቴሽናል ሳይንስ ፋኩልቲ፣

ሐ. የማህበራዊ ሳይንስ ፋኩልቲ፣

መ. የቋንቋና ሥነ-ሰብ ፋኩልቲ፣

ሠ. በቦርዱና በከተማ አስተዳደሩ የሚቋቋሙ ሌሎች ፋኩልቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ትምህርት ቤቶችና ተቋማት።

፫. አግባብነት ባላቸው የአዋጁ አንቀጽ ፹፰ ድንጋጌዎች ለሚኒስቴሩ □ተሰ□ እንዲሁም አንቀጽ ፵፬ ድንጋጌዎች ለቦርዱ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተጠሪነቱ ለከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ይሆናል፡፡

**፬. □ላማ**

የአዋጁ አንቀጽ ፬ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የከተማ አስተዳደሩን እንዲሁም ሀገሪቱን በተለያዩ ሙያዎች ሊያገለግል የሚችል ሕገ-መንግሥታዊ መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ የሚያውቅ የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት ማፍራት፣

## PART TWO
## OBJECTIVES, ESTABLISHMENT, POWERS AND DUTIES OF THE UNIVERSITY COLLEGE

**3. Establishment**

1. The Kotebe University College hereinafter referred to as the "University College" is hereby established as an autonomous higher education institution having its own legal personality.
2. The University College shall comprise the following institutions, faculties and schools:
   a. College of Teacher Education;
   b. Faculty of Natural and Computational Sciences;
   c. Faculty of Social Sciences;
   d. Faculty of Languages and Humanity;
   e. Other faculties, colleges, schools and institutions to be established by the Board and the City Government.
3. Without prejudice to the powers and duties of the Ministry provided under the relevant provisions of Article 88 of the Proclamation and that of the board provided for under the relevant provisions of Article 44 of the Proclamation, the University College shall be accountable to the Education Bureau of the City Government.

**4. Objective**

Without prejudice to provisions of Article 4 of the Proclamation, the University College shall have the following objectives:

1. Produce skilled manpower in quantity and quality that understands clearly his constitutional rights and duties and that will serve the City Government and the Country in different professions;

፪. የዘር፣ የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የፖለቲካና የመሳሰሉት ልዩነቶች የማይደረግበት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት መስጠት፤

፫. ችግር ፈቺ የሆነና የከተማ አስተዳደሩን ብሎም የሀገሪቱን እምቅ ሀብት ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ትምህርታዊና ተቋማዊ ስርዓት መዘርጋትና ጥናትና ምርምር ማድረግ፤

፬. ከሀገሪቱና ከከተማ አስተዳደሩ ፍላጎትና ዕድገት ጋር የተጣጣመ የከፍተኛ ትምህርትና የኅብረተሰብ አገልግሎት መስጠት፤

፭. ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ተቋማዊ ስርዓት መዘርጋት፤

፮. በአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚመለከታቸውን አካላት ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ የአሳታፊነት ባህልን መፍጠርና ማሳደግ፤

፯. የአገሪቱን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ያማከሉ ጥናቶችንና አውደ ጥናቶችን በማካሄድ እንዲሁም ሥልጠናዎችን በመስጠት በሰዎች መካከል የመከባበር፣ የመቻቻልና አብሮ የመኖር ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብትና እንዲሰርጽ ማድረግ፤

፰. የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል የምክርና ሥልጠና አገልግሎት መስጠት።

## ፭. ሥልጣንና ተግባር

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. ፋኩልቲዎች፣ ኮሌጆችና ሌሎች የትምህርት ተቋሞችን አቋቁሞ የቅድመ ምረቃ (የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህርነት፣ የዲፕሎማና የመጀመሪያ ዲግሪ) እንዲሁም የድህረ ምረቃ ትምህርት ይሰጣል፤

2. Provide higher education services that are free from any discrimination on grounds of race, religion, sex, politics and other similar grounds;
3. Lay down problem solving educational and institutional system that enables to utlize potential resources of the country and undertake study and research;
4. Provide higher education and community services that are compatible with the needs and development of the Country and the City Government;
5. Lay down institutional system that ensures transparency and accountability;
6. Ensure the participation of all concerned bodies in administrative decision making process, create and promote participatory culture;
7. Develop and disseminate democratic culture of respect, tolerance and living together among the people by conducting researches and conferences focusing on the different Nations and Nationalities of the Country as well as by offering trainings;
8. Provide consultancy and training services on the basis of fees.

## 5. Powers and Duties

The University College shall have the following powers and duties:

1. By establishing faculties, colleges and other educational and research Institutes, offer undergraduate (Pre-School Teaching Certificate, Diploma and Bachelor Degree) and Post-Graduate education;

፪. የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማና ዲግሪ ይሰጣል፤ እንዲሁም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉ ሰዎች የአካዳሚክ ማዕረግና ሽልማት ይሰጣል፤

፫. ለሀገር ዕድገት ቅድሚያ በሚሰጥባቸው መስኮች የከተማ አስተዳደሩንና የአገሪቱን ዕቅዶች መሠረት ያደረገ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤

፬. ሴሚናሮች፣ አውደ ጥናቶችና ሲምፖዚየሞችን ያዘጋጃል፤ ያካሂዳልም፤

፭. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ አቻ ዩኒቨርሲቲዎች እና ኮሌጆች፣ የምርምር ተቋሞችና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አካላት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፤

፮. የማማከር የልዩ ሥልጠናና ሌሎች አግባብ ያላቸው አገልግሎቶች ለኅብረተሰቡ፣ ለከተማ አስተዳደሩና ለሌሎች ተቋማት ይሰጣል፤

፯. የትምህርት መጽሔቶችና ጋዜጦች ያሳትማል፣ ያሰራጫል፤

፰. ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ያስከፍላል፤

፱. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲. ዓላማውን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፮. <u>አካዳሚክና አስተዳደራዊ ነጻነትና ተጠያቂነት</u>**

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተቀመጠውን ሥራ ላይ ለማዋል የሚከተሉት ነፃነቶችና ተጠያቂነቶች ይኖሩታል፡-

፩.በሕግ የተደነገጉ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ እውቀትን ለመሻት፣ ለማበልፀግና ለማሰራጨት በአዋጁ አንቀጽ ፲፮፣ ፲፯ እና ፲፰ መሠረት የአካዳሚክ ነጻነት ይኖረዋል፤

2. Confer certificates, diploma and degrees, award, academic titles and prizes to those who have made commendable contributions;
3. Undertake studies and research in priority areas for the development of the country based on the plans of the City Government and the Country;
4. Organize and conduct seminars, workshops and symposia;
5. Establish relations with local and foreign sister Universities, research institutions, and other organizations having similar objectives;
6. Provide consultancy, special training and other appropriate services to the community, the city government and other institutions;
7. Publish and distribute academic journals and newsletters;
8. Charge appropriate fees for the services it renders;
9. Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;
10. Carry out such other activities as are necessary for the attainment of the objectives.

**6. <u>Academic Freedom, Administrative Autonomy and Accountability</u>**

To implement the provisions of Article 5 of this Regulation, the University College shall have the following academic freedom, autonomy and accountabilities**:**

1. Subject to limitations provided by law, the University College shall have academic freedom to search for, advance and disseminate knowledge according to the provisions of Articles 16, 17 and 18 of the Proclamation;

፪. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚከተሉትን ጉዳዮች በሚመለከት አስተዳደራዊ ነጻነት ይኖረዋል፡-

ሀ. የውስጥ አደረጃጀቱን የመወሰንና በጀቱንና የሰው ኃይሉን የማስተዳደር፤

ለ. ስርዓተ ትምህርት የመገምገምና የማሻሻል፣

ሐ. የምርምር ስትራቴጂ የመንደፍና የማስፈጸም፤

መ. ከዓላማው ጋር የሚሄድ የገቢ ማመንጫ ድርጅት የማቋቋምና ገቢዎቹን የመጠቀም፡፡

፫. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ዓላማውን በሚገባ ስለማሳካቱ በተለይም የሚከተሉትን ስለማረጋገጡ ተጠያቂነት ይኖርበታል፡-

ሀ. የሚያካሂዳቸው የትምህርትና የምርምር መርሃ ግብሮች ከሀገሪቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም ከአስተዳደሩ ፍላጎቶች ጋር የተጣጣሙና ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቁ መሆናቸውን፤

ለ. አጠቃላይ አሰራሩ ተቋማዊ ሆኖ በግልጽነትና በአሳታፊነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን፤

ሐ. የበጀትና ሀብት አደላደሉና አጠቃቀሙ ወጪ ቆጣቢ መሆኑን፤

መ. ሠራተኞቹ በሚያስመዘግቡት የግልና የጋራ ውጤት የሚለኩ መሆኑን፤

ሠ. የተዋጣለት ተቋማዊ የትምህርትና የፋይናንስ ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን፡፡

## ፯. የመረጃ ልውውጥ

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ፡-

፩. ቦርዱ በሚያጸድቀው የውስጥ መመሪያ መሠረት ከመንግሥታዊ ተቋማት፣ ከግል ተቋማት እና ከሌሎች አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፤

2. The University College shall have administrative autonomy with respect to the following:
   a. Defining its internal organization and the administration of its budget and personnel;
   b. Curriculum review and development;
   c. Formulating research strategy and conducting same;
   d. Establishing income generating enterprise and using its proceeds.

3. The University College shall be accountable for the fulfilment of its objectives and, in particular, for ensuring that:
   a. Its educational and research programs are in line with the country's policies and strategies as well as demands of the Government and meet international standards;
   b. Its activities are institutionalized, transparent and participatory;
   c. The allocation and utilization of its budget and resources are based on cost effectiveness;
   d. Its personnel are evaluated on the basis of individual and collective results;
   e. It has successfully institutionalized its educational and financial information system.

## 7. Information Exchange

The University College shall:

1. Exchange information with private and public institutions and other bodies in accordance with internal directive approved by the Board;

፪. ማንኛውም ከትምህርት ጋር የተያያዘ ምርምር የሚሠራ ሠራተኛ ወይም ተማሪ ጥያቄ ሲያቀርብለት መረጃ ይሰጣል ወይም መረጃውን እንዲያገኝ ይረዳል፤

፫. የምርምርና ጥናት ጽሑፎች ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተማሪዎች፣ ተመራማሪዎችና ሌሎች ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል፤

፬. የወጪ መጋራት ውል ተጠቃሚ ተመራቂ ዎችን ዝርዝር ከተሟላ መረጃ ጋር ለከተማ አስተዳደሩና ለፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በወቅቱ ያስተላልፋል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአመራር አካላት

### ፰. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ቦርድ

፩. በአዋጁ አንቀጽ ፵፭ መሠረት የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ቦርድ ተጠሪነቱ ለከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ሆኖ የከተማዉን አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሀላፊ፣ የሚኒስቴሩን የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ደኤታን አካቶ ሰብሳቢውን ጨምሮ በከንቲባው የሚሰየም ሰባት ድምፅ መስጠት የሚችሉ አባላት ይኖሩታል፤

፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚደንት ድምፅ የማይሰጥ የቦርዱ አባልና ጸሓፊ ይሆናል።

### ፱. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

፩. ቦር□ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ መሠረት የሚከተሉት ዋና ዋና ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

ለ. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ዕቅድ፣ በጀት፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ አደረጃጀት፣ የአስተዳደርና አሰራር ስርዓት፣ የውስጥ ደንብና የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን በሚመለከት የሚቀርቡለትን ሀሳቦች መርምሮ ማጽደቅና ተግባራዊነ ታቸውን ይከታተላል፤

2. Provided, upon request, a worker or a student who undertakes research relating to education with information or assist to have access thereto;

3. Make documents of research and studies available to students, researchers and other beneficiaries of the University College;

4. Transfer, with relevant information and in due time, the list of graduating students who have benefited from cost sharing agreements to the City Government and the Federal Revenue and Customs Authority.

## PART THREE
## EXECUTIVE BODIES OF THE UNIVERSITY COLLEGE

### 8. The University College Board

1. Based on the provisions of Article 45 of the Proclamation, the University College Board shall have seven voting members including the Head of Education Bureau of the City Government, Minister Deetat of Higher Education in the Ministry and the chairperson assigned by the Mayor;
2. President of the University College shall be nonvoting member and secretary of the Board.

### 9. Powers and Duties of the Board

1. The Board, according to Article 44 of the Proclamation, shall have the following major powers and duties:
   a. Follow up implementation of provisions of this Regulation;
   b. Examine, approve and follow up the implementation of proposals of institutional reorganization, organizational plans, policies, administration and academic programmes and internal regulations of the institution;

ሐ. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ፕሬዚደንት እና ምክትል ፕሬዚደንት ሹመት ለከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ በማቅረብ ያስጸድቃል፤

መ. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የስትራቴጂክ እቅድ፣ ዓመታዊ እቅድና በጀት መመርመር፣ ለሚመለከተዉ አካል እንዲቀርብ ማድረግና ሲጸድቅም ተፈጻሚነታቸውን መከታተል፤

ሠ. በአስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ እና ደንቦች መሠረታዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ዲስፕሊን፣ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የሚመለከት ፖሊሲ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ያጸድቃልም፤

ረ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ማቋቋሚያ ሕግ ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ለከተማ አስተዳደሩ ያቀርባል፤

ሰ. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

ሸ. የሴኔት ውሳኔዎችና የሚያወጣቸው የአካዳ ሚክ ሕጎች መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

ቀ. በፕሬዚደንቱ ወይም በሴኔት የተላለፉ ውሳኔዎች የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ተልእኮ የሚጎዱ ወይም የመንግስትን ፖሊሲ ወይም ከአዋጅ ወይም ሕገ-መንግስቱን የሚቃረኑ ሆነው ሲገኙ ውሳኔውን ያግዳል፤

በ. በሴኔቱ ተጣርቶ በሚቀርብለት መሠረት የፕሮፌሰርነትየማዕረግ ዕድገትን ያጸድቃል፤

ተ. ከፕሬዚደንቱ በሚቀርብ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ለትምህርት የሚያስከ ፍላቸውን የተለያዩ ክፍያዎች አይነትና መጠን፤ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ገቢ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ተከፋይ አበሎችን (የትምህርት ክፍል ሃላፊነትና የመሳሰሉትን)እንደ ተከታታይ ትምህርት ያሉ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎችንና የመሳሰሉትን ይወስናል፤

c. Nominate the President and vice President for approval to the Mayor of the City Government;

d. Review and submit strategic plans, annual plans and budget of the institution to the concerned body and supervise their implementation up on approval;

e. Cause, as necessary, the formulation of and approve policies regarding employment, promotion, discipline, salary, allowances, and other benefits for the administrative and technical support staff of the University College on the basis of the basic principles of the civil service laws of the city government;

f. Submit proposal, as may be necessary, to the city government for the amendment of the law establishing the University College;

g. Examine and give final decision on grievances against decision by the University College;

h. Monitor the implementation of senate legislations and decisions;

i. Rescind decisions made by the president or the senate when the decisions compromise the mission of the University College, contravene government policy, the Proclamation or the Constitution;

j. approve promotions to the rank of professorship up on recommendation of the Senate;

k. Determine upon advice by the president the type and amount of different payments relating to education charged by the University College, decide on payable allowances (for heads of academic units and so on) overload rateslike extension payments and other similar sundry rates;

ቸ. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ምክትል ፕሬዚደንት ኃላፊነቱን በመወጣት ረገድ ከፍተኛ የሆነ ድክመት ካሳየ ከኃላፊነት ማሰናበትን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፣ ፕሬዚደንቱን የሚመለከት ሲሆን ደግሞ ለከንቲባው አስተያየት በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

፪. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎችና ምልዓተ ጉባኤ በአዋጁ አንቀጽ ፵፭ እና ፵፮ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፲. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሴኔት

ሴኔቱ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚደንት ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚዳንት……………ሰብሳቢ፣
፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ምክትል ፕሬዚደንቶች….አባል፣
፫. የአካዳሚክ ፕሮግራም ዳይሬክተር ……..…. አባል፣
፬. የፋኩልቲ፣ ኢንስቲትዩት፣ የትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች ዲኖች……………………..........……አባል፣
፭. የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክተር…አባል፣
፮. የተከታታይና የርቀት ትምህርት ፕሮግራም ዳይሬክተር……………………………….....አባል፣
፯. የሕዝብና የውጭ ግንኙነት ዳይሬክተር …….አባል፣
፰. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሬጅስትራር…….አባልና ፀሐፊ፣
፱. የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር….…........አባል፣
፲. የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር …......................………………………….አባል፣
፲፩. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ተወካይ…………………………….……...አባል፣
፲፪. ሁለት የአካዳሚክ ሠራተኞች ተወካዮች…….አባል፣
፲፫. ሁለት የተማሪዎች ተወካዮች/ቢያንስ አንዱ ሴት/ ……………………………………….……አባል፣

l. Take, without prejudice to the applicability of other relevant laws, any disciplinary action, including removal from office, against any vice president in the event of serious failure to discharge his responsibility; in the case of the President, consult the Mayor for measures to be taken;

2. Regular sessions and quorum of the board shall be effected in accordance with Articles 45 and 46 of the Proclamation.

## 10. The University College Senate

The Senate, being accountable to the University College President, shall have the following members:

1. President of the University College…...Chairperson;
2. Vice Presidents of the University College ..……….. ……………………………………..……..Member;
3. Academic Program Director ….................Member;
4. Deans of Faculties, Institutes, Schools and Colleges …….............……………………………..Members;
5. Education Quality Assurance Director …..Member;
6. Continuing and Distance Education Program Director……………...……………........Member;
7. Public and External Relations Director….. Member;
8. Registrar of the University College ...........................................Member and Secretary;
9. Students' Service Director .……….……..Member;
10. Research and Community Service Director ……………….………..…………… Member;
11. Gender Affairs Officer of the University College …………………..…...…………………...….Member;
12. Two representatives of the Academic Staff ……………………….…………………..… Members;
13. Two Students representatives (at least one being female)………..…………………………Members.

**፲፩. የሴኔቱ ሥልጣንና ተግባር**

በአዋጁ አንቀጽ ፵፱ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሴኔቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በቦርዱ የሚወጡ አጠቃላይ መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪. የተማሪዎች አቀባበልን፣ የደረጃ አወሳሰንን፣ የዲስፕሊን ጉዳዮችንና ምረቃን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት፣ እነዚህኑ በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ይወስናል፤

፫. አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥና ደረጃዎች አቅጣጫዎችን ይወስናል፤

፬. ሕጎችንና በቦርድ የሚወጡ ፖሊሲዎችን መሠረት በማድረግ የተማሪዎች አስተዳደርን፣ የትምህርት ነክ ጉዳዮችን፣ የትምህርት ኃላፊዎች አመራረጥን እና የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ዲስፕሊንና ደመወዝ በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤

፭. የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለቦርዱ ሃሳብ ያቀርባል፤

፮. የረዳትና የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ይሰጣል፤

፯. የሙሉ ፕሮፌሰር አዲስ ቅጥር በመመርመር ያጸድቃል፤

፰. ፕሬዚደንቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ መቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በየሩብ ዓመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤

፱. ተግባሩን ለሌሎች የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካላትና ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎች በውክልና ያስተላልፋል፤

፲. በቦርዱ የሚሰጡትን ወይም በፕሬዚደንቱ የሚመሩለትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

**11. Powers and Duties of the Senate**

Subject to the provisions of Article 49 of the Proclamation, the Senate shall have the powers and duties to:

1. Implement directives issued by the Board;
2. Set criteria for admission of students, determination of academic standards, disciplinary measures and graduation, and to examine and decide on petitions relating thereto;
3. Determine general directions for conducting examinations and grading;
4. Issue directives on the basis of laws and policies adopted by the Board, on student administration, academic matters, procedure for selection of academic heads and on employment, promotion, fringe benefits, discipline and salary of academic staff;
5. Propose awarding of promotion of professorships to the Board;
6. Award promotions of assistant and associate professorships;
7. Examine and approve the employment of full professor of the University College;
8. Without prejudice to the power of the president to call a meeting at any time where he deems it necessary, convene a meeting at least once every quarter;
9. Delegate its duties to other bodies and standing or ad-hoc committees of University College;
10. Perform such other activities as may be assigned to it by the Board or forwarded to it by the President.

፲፪. <u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንቶች</u>

፩. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ዕጩ ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንቶች ሆነው የሚቀርቡ ሰዎች የተመሰከረለት የአካዳሚክ መሪነትና የአስተዳደር ክህሎት እንዲሁም ለተቋማዊ ለውጥና ዕድገት ዝግጁ የሆኑና ሕገ-መንግሥቱንና የመንግስት ፖሊሲዎችን የተቀበሉ መሆን ይኖርባቸዋል፣

፪. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ለፕሬዚደንቱ ተጠሪ የሆኑ ሁለት ምክትል ፕሬዚደንቶች ይኖሩታል፣

፫. የዩኒቨርስቲ ኮሌጁ ፕሬዚደንትም ሆነ ምክትል ፕሬዚደንቶች በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተራ ፊደል (መ) መሠረት በቦርዱ አቅራቢነት በከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ይሾማሉ፣

፬. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚደንት የአገልግሎት ዘመን ስድስት ዓመት ሲሆን የምክትል ፕሬዚዳንቶች አራት ዓመት ይሆናል፣ ሆኖም የአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በተደጋጋሚ ሊሾሙ ይችላሉ፣

፭. ማንኛውም ተጠባባቂ ፕሬዚደንት ወይም ተጠባባቂ ምክትል ፕሬዚደንት ከ፩፻፹ ቀናት በላይ ተጠባባቂ ፕሬዚደንት ወይም ተጠባባቂ ምክትል ፕሬዚደንት ሆኖ መቆየት የለበትም፣

፮. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚደንት በአዋጁ አንቀጽ ፶፫ የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፯. ፕሬዚደንቱ ሙሉ ጊዜውን ለቢሮው ሥራዎች ያውላል፣

፰. ፕሬዚደንቱ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሥራው ላይ በማይገኝበት ጊዜ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚደንቱን ተክቶ ይሠራል፣ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚደንቱ የማይገኝ ቢሆን ግን የአስተዳደር ምክትል ፕሬዚደንትን ሊወክል ይችላል፡፡

12. <u>**President and Vice Presidents of the University College**</u>

1. The candidate president and vice president of the University College shall have, among others, commendable academic leadership and managerial ability as well as demonstrable commitment to institutional change and development and loyal to the Constitution and government policies;
2. The University College shall have two Vice Presidents who shall be accountable to the president;
3. The president of the University College as well as the vice presidents shall be appointed by the Mayor of the City Government in accordance with sub-article (1)(d) of Article 44 of the Proclamation based on the Board's recommendation;
4. The term of office of the president of the University College shall be six years and that of the vice presidents shall be four years; provided however, that and without prejudice to other provisions of the Proclamation, they may be repeatedly reappointed;
5. No person shall hold the position of acting president or acting vice president for a period of more than 180 days;
6. The powers and duties of the President of the University College shall be as provided in Article 53 of the Proclamation;
7. The President shall devote full time to the requirement of his office;
8. In case of absence from duty, the Academic Vice President shall act on his behalf and, in case of simultaneous absence of the said vice president, the Administrative vice president shall be delegated.

**፲፫. <u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ምክትል ፕሬዚደንቶች ሥልጣንና ተግባራት</u>**

፩. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአካዳሚክና ምርምር ምክትል ፕሬዚደንት በአዋጁ አንቀጽ ፶፬ ከተደነገገዉ በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. በቦርዱና በሰኔቱ የተላለፉ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ በማዋል ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ ክፍሎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ፋኩልቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ተቋሞች ትምህርት ቤቶች እና የተከታታይ ትምህርት ክፍሎችን ሥራ ያቅዳል፣ ይመራል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፤

ሐ. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የምርምርና ጥናት እንቅስቃሴዎችን ያቅዳል፣ ይመራል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፤

መ. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ቤተ መጻሕፍት፣ ሬጅስትራር ጽሕፈት ቤትና ሌሎች በሥሩ ያሉትን ክፍሎች ይመራል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፤

ሠ. በዘርፉ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶችንና ትብብሮችን ያፈላልጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ረ. በስሩ ያሉ ክፍሎችን የሥራ አፈጻጸም፣ የበጀት ክፍፍልና አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ሪፖርት ለፕሬዚደንቱ ያቀርባል፤

ሰ. በቦርዱ፣ በሴኔቱና በፕሬዚደንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**13. <u>Powers and Duties of Vice Presidents of the University College</u>**

1. The Academic and Research Vice President of the University College shall, in addition to the powers and duties stated in Article 54 of the Proclamation:

a. Implement decisions and directives of the Board and the Senate in directing and supervising the activities of organs of the University College accountable to him;

b. Plan, direct and supervise the activities of faculties colleges, institutes, schools and continuing education programs of the University College;

c. Plan, direct and supervise research and studies activities of the University College;

d. Direct and supervise the library, office of the registrar and other organs of the University College which are directly accountable to him;

e. Solicit national and international links and partnerships, and follow their implementation in his division;

f. Report to the President on the performance budget allocation and utilization and other activities of the units under him;

g. Carry out other activities which may be specifically entrusted to him by the Board, the Senate and the President.

፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚደንት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአስተዳደርና የልማት ጉዳዮችን በተመለከተ ፕሬዚዳንቱን ያማክራል፤

ለ. የተማሪዎች አገልግሎትን፣ የፋይናንስን፣ የአስተዳደርና የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲሁም ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ. በቦርዱና በሴኔቱ የተሰጡ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ. በስሩ ያሉ ክፍሎችን የሥራ አፈጻጸም፣ የበጀት ክፍፍልና አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ሪፖርት ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤

ሠ. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አዳዲስ የቢዝነስ ሃሳቦችንና ልማትን ያቅዳል፤

ረ. የዩኒቨርሲቲው ኮሌጁን አዳዲስ የልማትና የማስፋፋት የካፒታል ኢንቨስትመንቶችን ያቅዳል፣ ያስተዳድራል፤

ሰ. ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የተገናኙና እርሱን የሚመለከቱ ስምምነቶችና ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይመራል፤

ሸ. የቢዝነስና የስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ለፕሬዚደንቱ ያቀርባል፤

ቀ. ሌሎች ከቦርዱ፣ ከሴኔቱና ከፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

2. The Administration and Development Vice-President of the University College shall:

a. Consult the President with regard to the administrative and development activities of the University College;

b. Direct and supervise the University College students' service, financial, administrative and support services as well as the activities of other organs of the University College accountable to him;

c. Implement decisions and directives issued by the Board and the Senate;

d. Report to the president on the performance, budget allocation and unitization and other activities of the units under him;

e. Plan direct and supervise new venture and development activities in the University College;

f. Plan and manage capital investments of the University that are related to new developments and expansions;

g. Direct the implementation of agreements entered with other institutions and projects connected with activities falling within his mandates;

h. Prepare and submit business and strategic plans to the president;

i. Carry out other activities which may be specifically entrusted to him by the Board, the Senate and the President.

## ፲፬. የአስተዳደር ጉባዔ

፩. ፕሬዚደንቱ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ኃላፊዎች ለመጨመር ያለው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዚደንቱ፣ ምክትል ፕሬዚደንቶቹ እና የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር የአስተዳደር ጉባዔው ዋናዎቹ አባላት ይሆናሉ፤

፪. የአስተዳደር ጉባዔው በስትራቴጂክ ጉዳዮች እና ፕሬዚደንቱ በጋራ እንዲታዩ በሚያምንባቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጣል፣ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን መከታተያ የማስተባበሪያና የመገምገሚያ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፤

፫. የአስተዳደር ጉባዔው ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ እንዲሁም የአስተዳደር ካውንስሉ ቃለ ጉባዔ ፕሬዚዳንቱ በሚመድበው ጸሐፊ ይያዛል፤

፬. አስተዳደር ጉባዔው ከመደበኛ አባላቱ አብላጫው ሲገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

## ፲፭. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባዔ

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በአዋጁ አንቀጽ ፶፯ መሠረት የተቋቋመ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ካውንስል የሚኖረው ሲሆን ካውንስሉም የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባኤ በፕሬዚደንቱ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ አባላቱ የአስተዳደር ጉባዔው ዋናዎቹ አባላት፣ የአካዳሚክ ክፍሎች ኃላፊዎች፣ የሴኔት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የቤተመጻሕፍት እና ዶክመንቴሽን ኃላፊ፣ የሬጅስትራር፣ የአገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ኃላፊዎች እና በፕሬዚደንቱ ምክር ላይ ተመስርቶ ቦርዱ በሚወስነው መሠረት የጾታ ተዋጽኦውን የጠበቀ የአካዳሚክ ሠራተኞችና ተማሪዎች ተወካዮች ይሆናሉ፤

## 14. Managing Council

1. Without prejudice to the power of the president to include other pertinent officers, the president, the vice presidents, and the students' service director shall constitute the core members of the managing council;

2. The managing council discuss and pass decision on strategic and other issues the president believes to be decided jointly; as well serve as forum for follow up, coordination and evaluation of the University College;

3. The managing council shall meet regularly at least twice a month; and minutes of sessions of the managing council shall be taken by a secretary designated by the president;

4. There shall be quorum of the managing council where majority of its core members are present.

## 15. University College Council

The University College shall have a University College council established in accordance to Article 57 of the proclamation with the following duties and responsibilities፡

1. The president shall chair the University College council, and its members shall consist of the core members of the managing council, heads of academic units, members of the senate standing committee, the library and documentation head, the registrar, service department heads, and as it shall be determined by the board upon the advice of the president, an appropriate number of academic staff and student representatives with appropriate gender mix;

፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባኤ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ረቂቅ ዕቅድ፣ በጀት፣ አደረጃጀትና መመሪያዎች፣ የትምህርት ፕሮግራሞች፣ የትብብርና የግንኙነት ስምምነቶች፣ በትምህርት ክፍሎች መከፈል፣ ውህደትና መዘጋት እንዲሁም በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ላይ ሀሳብ በመስጠት ፕሬዚደንቱን ያማክራል፤

፫. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባኤ መደበኛ የስብሰባ ቀንና ሠዓት ኖሮት ቢያንስ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤

፬. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባኤ ስብሰባ ላይ የአባላቱ መገኘት ግዴታ ነው፤ በፕሬዚዳንቱ ፍቃድ ካልሆነ በስተቀር አባልነት በውክልና ሊሰጥ አይችልም፤ ስብሰባዎች ያለምልአተ ጉባኤ ሊካሄዱ ይችላሉ፤

፭. ፕሬዚደንቱ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ጉባኤው ስብሰባ ሂደት ሃሳብን በነጻ ለመግለጽ የሚያበረታታ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ መኖሩን ያረጋግጣል፤ በጉባኤው ውይይት ሰፊ የሃሳብ ልዩነት የተንፀባረቀ ከሆነ የሃሳቦቹን ክብደት ለማወቅ ሲባል ፕሬዚደንቱ በጉዳዩ ላይ ድምፅ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል፤

፮. የአስተዳደር ካውንስሉ ጸሐፊ ድምጽ የማይሰጥና ውይይቱ ላይ የማይሳተፍ ጸሐፊ ሆኖ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በጉባኤው ያገለግላል፤

፯. ከፕሬዚደንቱ ወይም ፕሬዚዳንቱ ከሰየመው ሰው ውጪ ማንኛውም አባል የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባኤው ቃል አቀባይ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፤

፰. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባኤው የራሱን የአሰራር ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2. The University College council shall advise the president by expressing its views on institutional proposals regarding plans, budget, organizational structures, academic programmes, agreements of cooperation, and on division, merger and closure of academic units as well as on performance;
3. The University College council shall have a fixed day and time for meeting and shall meet at least once every six months;
4. Attendance of University College council sessions by members shall be mandatory. Membership shall not be delegated except in accordance with the permission of the president. Sessions may be held without a requirement for quorum;
5. The president shall ensure a democratic atmosphere stimulating free expression of opinions and ideas in sessions of the University College council. The president may order votes in case substantially competing opinions emerge to ascertain the weight of the competing opinions;
6. The secretary of the managing council shall also serve as the non-voting and non-consultative secretary of the University college council;
7. No member of the University College council other than the president or a person nominated by the president shall serve as its official spokesperson;
8. Without prejudice to the provisions of this Article, the University College council may adopt its own rules of procedures.

## ፲፮. የአካዳሚክ ኮሚሽን

፩. እያንዳንዱ ፋኩልቲ፣ ኮሌጅ፣ ኢንስቲትዩት ወይም ትምህርት ቤት ለዲኑ ተጠሪ የሆነ የራሱ አካዳሚክ ኮሚሽን ይኖረዋል፡፡

፪. የአካዳሚክ ኮሚሽን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. የፋኩልቲው፣ የኮሌጁ፣ የኢንስቲትዩቱ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲን ……………..ሰብሳቢ፤

ለ. የፋኩልቲው የኮሌጁ፣ የኢንስቲትዩቱ ወይም የትምህርት ቤቱ ረዳት ዲኖች ካሉ..አባላት፤

ሐ. የዲፓርትመንት ኃላፊዎች ………..አባላት፤

መ. አንድ የተማሪዎች ተወካይ ………..አባል፤

ሠ. አንድ የመምህራን ተወካይ…………..አባል፤

ረ. የፋኩልቲው የተከታታይ ትምህርት አስተባባሪ ……………………..…..አባል፤

ሰ. የፋኩልቲው ረዳት ሬጅስትራር …… አባል፤

ሸ. በአካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚመደቡ አግባብነት ያላቸው ሌሎች ኃላፊዎች……..…..አባላት፤

፫. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሴኔት የሚያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ አካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ. የፋኩልቲውን፣ የኮሌጁን፣ የተቋሙን ወይም የትምህርት ቤቱን ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

ለ. የሥልጠናና የትምህርት መርሀ ግብሮችን ሥርዓተ ትምህርቶች አዘጋጅቶ በሴኔቱ ያስጸድቃል፤

ሐ. በሴኔቱ መመሪያ መሠረት የተማሪዎችን ትምህርትና ስነ-ምግባር የተመለከቱ ዝርዝር መስፈርቶችን ይወስናል፤

መ. የክብር ዲግሪና ከትምህርት ጋር የተያያዙ ሽልማቶች እንዲሰጡ ለሴኔቱ ሃሳብ ያቀርባል፤

## 16. Academic Commission

1. Each faculty, College, institute or school shall have its own academic commission accountable to the dean.
2. The academic commission shall have the following members:
   a. Dean of the Faculty, College, School or Institute ……………...……. Chairperson;
   b. Associate Deans of the Faculty, College, School or Institute (if any)…… Members;
   c. Head of Departments ………..…Members;
   d. A representative of students….… Member;
   e. A representative of the academic staff..Member;
   f. Continuing education coordinator of the faculty …..……………………..Member;
   g. Associate registrar of the faculty…….Member;
   h. Other appropriate officers to be designated by the academic commission…...Members;
3. Subject to directives of the Senate the academic commission shall have the following powers and duties:
   a. Plan activities of the faculty, college, institute or school and prepare budget and follow up the implementation of same;
   b. Prepare curricula of training and educational programs and submit same to the Senate for approval;
   c. Set educational and disciplinary standards of students in conformity with directives of the Senate;
   d. Recommend to the Senate the awarding of honorary degrees and education related prizes;

ሠ. የሌክቸረር፣ ረዳት ሌክቸረር፣ ረዳት ምሩቅና የቴክኒክ ረዳቶችን ዕድገት በሴኔት መመሪያ መሠረት አጣርቶ ይወስናል፤

ረ. የተባባሪና ረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለሴኔቱ ሀሳብ ያቀርባል፤

ሰ. የአካዳሚክ ሠራተኞች ቅጥርን ይመረምራል፣ ከዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ዕቅድ ጋር በተጣጣመ መልኩ የነጻ ትምህርት ዕድል፣ የምርምርና ሰባቲካል ዕረፍቶችን ያጸድቃል፤

ሸ. የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት ደንብ ይወስናል፣

ቀ. ከሴኔቱና ከፕሬዚደንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

e. Examine and decide, in accordance with directives of the Senate, on the awarding of academic promotion to the positions of lecturers, assistant lecturers, graduate assistants and technical assistants;

f. Recommend to the Senate the awarding of the academic promotions of associate and assistant professorships;

g. Examine the recruitment of the academic staff, and decide on cases of scholarships and research and sabbatical leaves based on the plan of the University College;

h. Adopt its own rules of procedures for conducting meetings;

i. Perform other activities as may be assigned to it by the president and the Senate.

## ፲፯. <u>የዲፓርትመንት ጉባዔ</u>

፩. እያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ዲፓርትመንት የራሱ ጉባኤ ይኖረዋል፡፡

፪. የዲፓርትመንት ጉባዔ በዲፓርትመንቱ ኃላፊ የሚመራ ሆኖ ሁሉንም የሙሉ ጊዜ መምህራንን ያካትታል፡፡

፫. የዲፓርትመንት ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. በዲፓርትመንቱ የሚሰጠውን የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ የሚያስገኙ መርሃ ግብሮችን ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ያስፈጽማል፤

ለ. የዲፓርትመንቱን ዓመታዊ እቅድ፣ በጀትና ሪፖርት ያዘጋጃል፤

ሐ. የዲፓርትመንቱን የሰው ኃይልና ፋይናንስ አስተዳደር ይከታተላል፤

መ. የመምህራንና የተማሪዎችን ክትትልና ግምገማ ያከናውናል፤

## 17. <u>Department Assembly</u>

1. Each department of the University College shall have its own department assembly;
2. Every department assembly shall be composed of all fulltime academic staff members of the department and shall be chaired by the head of the department;
3. A department assembly shall have the following powers and duties:

a. Submit recommendations to the academic commission on the programs of studies necessary for obtaining certificates, diplomas or degrees offered by the department and implement same upon approval;

b. Prepare the annual plan, budget and reports of the department;

c. Monitor the financial and personnel management of the department;

d. Conduct teachers' and students' appraisal and evaluation;

ሠ. ፈተናዎችንና የአካዳሚክ ግምገማ ስርዓትን ደረጃ ያወጣል፣ ይከታተላል፤

ረ. የማስተማሪያ ጽሑፎችን አመራረጥና ዝግጅት ይወስናል፣ የመምህራን የሥራ ጫናና ድልድል ይወስናል፤

ሰ. በስርዓተ ትምህርትና በመማር ማስተማር ስርዓት ማሻሻያዎችና ፈጠራዎች እንዲጎለብቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሸ. የተማሪዎችን ውጤት ያጸድቃል፤

ቀ. ሌሎች በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የበላይ ኃላፊዎች በፋኩልቲው ዲን፤ እንዲሁም በትምህርት ክፍሉ ኃላፊ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፲፰. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ልዩ ልዩ ክፍሎች የውስጥ አሰራር ነጻነት**

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ የተዘረዘሩት የዩኒቨር ሲቲ ኮሌጁ አካላት ድርጅታዊ መዋቅር በቦርዱ ይጸድቃል፤

፪. እያንዳንዱ ፋኩልቲ፣ ተቋም፣ ትምህርት ቤት ወይም ኮሌጅ በተግባራቱና በበጀት አጠቃቀሙ ዙሪያ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ማግኘት እንዲችል የበጀት ማዕከል ደረጃ ሊኖረው ይችላል፤

፫. እያንዳንዱ የበጀት ማዕከል የራሱን ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ የበጀትና ሀብት አጠቃቀምን ይወስናል፣ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፡፡

**፲፱. ለአመራር ቦታዎች የሚጠየቁ መስፈርቶች**

በዩኒቨርስቲ ኮሌጁ ዉስጥ ያሉ አካላትን ለመምራት በዕጩነት የሚቀርብ ሰዉ በተለይ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

፩. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ቋሚ የአካዳሚክ ሠራተኛ ሆኖ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት ያገለገለና ቢያንስ የሌክቸረር አካዳሚክ ማዕረግ ያለው፤

e. Standardize and supervise examination and academic evaluation systems;

f. Determine teaching material selection and preparation to courses, and approve distribution of teaching load to staff members;

g. Support and facilitate quality improvement and innovation in curriculum and learning teaching systems;

h. Approve students' grades;

i. Perform other activities assigned to it by executive officials of the University College, the faculty dean and head of the department.

**18. Internal Autonomy of Organs of the University College**

1. The organizational structures of the various organs of the University College referred to in Article 3 of this Regutation shall be approved by the Board;
2. Each faculty, institute, school or college may have a cost center status for a close monitoring and support on its activities and its budget utilization;
3. Each cost center shall prepare its own action plan and budget, decide on the utlization of budget and resources and prepare reports.

**19. Qualification Requirement for Leadership Posts**

A cadidate nominated to serve as head of any organ of the University College shall meet the following qualification requirements፡

1. Shall be fulltime academic staff member with at least two years service in the University College with a minimum academic rank of lecturership;

፪. የሥራ አመራር ብቃት ያለው፤

፫. በተቋሙ የአካዳሚክ፣ የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ውስጥ ብቁ ተሳትፎ ያለው፤

፬. ውጤታማ ሥራ የሠራና መልካም ስነ-ምግባር ያለው፡፡

## ክፍል አራት
## ስለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሠራተኞችና ተማሪዎች

### ፳. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሠራተኞች

፩. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ የተመለከቱት ሠራተኞች ይኖሩታል፤

፪. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ እና ቦርዱ በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት የሌላ መንግሥታዊ ወይም የግል ተቋም አካዳሚክ ሠራተኛን በጋራ ቅጥር ማሰራት ይችላል፤

፫. የጋራ ቅጥሩ በቅድሚያ የሌላው ቀጣሪ ፈቃደኛነት ተጠይቆ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁና በግለሰቡ መካከል በሚደረግ ውለታ መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፤

፬. በጋራ የተቀጠረው ባለሙያ እንደቋሚ መምህር የሚታይ ሆኖ በሕግ የተመለከቱ ግዴታና መብቶች ይኖሩታል፤

፭. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሠራተኞች መብትና ግዴታ በአዋጁ አንቀጽ ፴፩፣ ፴፪፣ ፴፫ እና ፴፮ የተመለከተው ይሆናል፡፡

### ፳፩. የተማሪዎች መቀበያ መመዘኛ

፩. በዚህ ደንብና በሌሎች ሕጎች ስለመቀበያ መመዘኛ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በመደበኛም ሆነ በተከታታይ ትምህርት መርሀ ግብሮቹ፡-

2. Effective leadership competence;
3. Demonstrated effective participation in the academic, research and community service of the University College;
4. Demonstrated results and good conduct.

## PART FOUR
## STAFF AND STUDENTS OF THE UNIVERSITY COLLEGE

### 20. The University College Staff

1. The University college shall have staff as provided in Article 29 of the proclamation;
2. The University College may, in accordance with Article 44 of the Proclamation and directives of the Board, engage a staff of another government or private instituation on the basis of joint employment;
3. The joint employment shall be effected by concluding a contract between the University College and the individual upon obtaining the prior consent of the other employer;
4. The joint employee shall be considered as a full time academic staff and shall have the rights and obligations provided by law with respect to such staff;
5. The University College staff shall have the rights and obligations as provided in Articles 31, 32, 33 and 36 of the Proclamation.

### 21. Admission of Students

1. In both its regular and continuing education programs without prejudice to the provision of this Regulations and other relevant laws regarding the requirements of admission of students, the University college፡

ሀ. ተገቢውን መመዘኛ ላሟሉ ትዮጵያውያን ያለምንም ልዩነት ክፍት ይሆናል፣

ለ. ለቅድመ መደበኛ ምስክር ወረቀት መርሀ ግብር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወይም የውጭ አገር ተመጣጣኝ ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎችን ሴኔቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ተቀብሎ ያስተናግዳል፣

ሐ. ለዲፕሎማ መርሃ ግብር የአጠቃላይ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ወስደው ያለፉ ወይም የውጭ አገር ተመጣጣኝ ትምህርት ያጠናቀቁ ሆነው የሚኒስቴሩን መስፈርት እና የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የመግቢያ መመዘኛ ያሟሉ ተማሪዎችን ተቀብሎ ያስተናግዳል፣

መ. የኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ወይም ሚኒስቴሩ በሰጠው ግምት ተመጣጣኝ የሆነ የውጭ ሀገር ሁለተኛ ደረጃን ያጠናቀቁ ሆነው የሚኒስቴሩን መስፈርት እና የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የመግቢያ መመዘኛ ያሟሉ ተማሪዎችን ለቅድመ ምረቃ ዲግሪ መርሃ ግብር ትምህርት ተቀብሎ ያስተናግዳል፣

ሠ. ለዲፕሎማ (፲፪+፪) ወይም (፲+፫) ደረጃ ያላቸው ተማሪዎችን በሚኒስቴሩ መመሪያ መሠረት በቅድመ ምረቃ ዲግሪ መርሃ ግብር ሊቀበል ይችላል፣

ረ. የከፍተኛ ትምህርት የቅድመ ምረቃ ዲግሪ ትምህርት ያጠናቀቀና የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የመግቢያ መመዘኛዎችን ያሟላ ተማሪን ለድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር ትምህርት ይቀበላል፣

a. Shall be open to all qualified Ethiopians without any discrimination;

b. Shall admit, for Pre-school Teaching certificate studies, students who have completed Ethiopian General Secondary School education or foreign equivalent education in accordance with directives of the Senate;

c. Shall admit, for diploma program studies, students who have completed Ethiopian General Secondary School education with pass marks or foreign equivalent level as determined by the Ministry and satisfy its entrance qualification requirements;

d. Shall admit, for undergraduate studies, students who have completed Ethiopian preparatory level school education or foreign equivalent level as determined by the Ministry and satisfy its entrance qualification requirements;

e. May admit students with diploma (12+2 or 10+3) in accordance with the rules of the Ministry in its undergraduate program;

f. Shall admit, for post graduate studies, students who have completed their undergraduate studies and satisfy its entrance qualification requirements;

ሰ. ለሴቶች፣ ለታዳጊ ክልል ብሔረሰብ እንዲሁም ለጎልማሳና ልምድ ላላቸው ተማሪዎች የትምህርት ሚኒስቴር በሚያወጣው የተለየ የአቀባበል ስርዓት መሠረት ሊወሰን ይችላል፡፡

፪. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚቀበለው ተማሪ በወጪ መጋራት መርህ መሰረት ያለበትን ግዴታ የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

፫. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የተማሪውን ችሎታና የዕውቀት ደረጃ እንዲሁም ክህሎት ለመገምገም የሚያስችል መመዘኛ ያዘጋጃል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጥ መመዘኛ ለተማሪው በተሰጠው ትምህርት ወይም ሥልጠና ይዘት ላይ የተመሰረተ ተከታታይ ምዘና መሆን አለበት፡፡

፭. መመዘኛው የሚሰጥበት መንገድ በቃል፣ በጽሑፍ፣ በተግባርና ሌሎች ሴኔቱ በሚወሰንባቸው መንገዶች ሊሆን ይችላል፡፡

፮. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የምዘና ውጤቶችና የፈተና ወረቀቶችን ለተማሪው መመለስ ወይም በግልጽ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፪. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳ ዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

g. May determine according to Ministry of Education especial admission procedures for female students, students from developing regions, adults and experienced students.

2. Any student admitted by the University College shall be obliged to fulfill the requirements of principles of cost sharing.

3. The University College shall design an assessment mechanism that enables it to evaluate the ability and level of knowledge as well as skills of its students.

4. The methods of assessment designed in accordance with sub article (3) of this Article shall be based on the content of course or training offered to the student and based on continuos assessment.

5. The methods of assessment may be oral, written, practical or any other form as determined by the Senate.

6. The University College shall return the results and examination papers to students or make a transparent notification of same.

## PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 22. Inapplicable Laws

No regulation, directive, or traditional practice shall in so far as it is inconsistent with the provisions of this Regulation, be applicable with respect to matters provided for by this Regulation.

**፳፫. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>**

ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በመባል የሚታወቀው ተቋም መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተላልፈዋል፡፡

**፳፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከመስከረም ፳፬ ቀን ፪ሺ፮ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**መስከረም ፳፫ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**23. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>**

The rights and obligations of the insritution known as the Kotebe College of Teacher Education are hereby transferred to the University College.

**24. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall be effective as of 4th day of October, 2013.

**Done at Addis Ababa**
**On this Day of 3rd October, 2013**

**Diriba Kuma**
**Mayor of Addis Ababa City**